# የምልጃ ጸሎት



ከእናንተ ማንኛውም ወዳጅ ያለው በእኩለ ሌሊትስ ወደርሱ ሄዶ፤- ወዳጄ ሆይ ሶስት እንጀራ አበድረኝ፣ አንድ ወዳጄ ከመንገድ ወደኔ መጥቶ የማቀርብለት የለኝምና ይላልን? ያም ከውስጥ መልሶ፤- አታድክመኝ፣ አሁን ደጁ ተቆልፏል፣ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ፣ አሁን ልሰጥህ አልችልም ይላልን? እላችኋለሁ ወዳጅ ስለሆነ ተነስቶ ባይሰጠው እንኳ ስለንዝነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል። እኔም እላችኋለሁ፤- ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፣ መዝጊያን አንኳኩ ይከፍትላችሁማል። ሉቃስ 11፡5-7

ከላይ ያነበብነው የወንጌል ክፍል ስለ ምልጃ ጸሎት የሚያስተምረን ዋና ፍሬ ነገር አለው። ይኸውም የምንማልድለትን ነገር ማወቅ፣ ጊዜን ምክንያት አለማድረግ፣ ወደ ጌታ ፊት  መቅረብና ያለማቋረጥ ማንኳኳት ናቸው። አነዚህም በሚቀጥሉት አራት ዋና ዋና ፍሬ ቃሎች ተገልጸዋል።

ሀ. <u>ወዳጁ ማነው?</u>

ወዳጄ ማነው? ብሎ ለጠየቀው ሰው የጌታ ኢየሱስ መልስ በወንበዴዎች ተመትቶ ስለወደቀው ሰውና ስለደጉ ሳምራዊ ሰው መተረክ ነበር። ይኸንን በወንበዴ የተጎዳ ሰው ካህኑና ሌዋዊው አልፈውት ሄዱ፣ ያ ሳምራዊ ግን ከወደቀበት አንስቶ ቁስሎቹን ጠገነለት፣ በራሱ አህያ ጭኖ ወደማረፊያ ቤት ወሰደው ያለውን ገንዘብ ሁሉ ከፈለለት። ከዚያው በማያያዝ ጥያቄውን ወደ ጠያቂው በመመለስ ከነዚህ ከሶስቱ ለወደቀው ሰው ማን ይመስልሀል ወዳጁ? አለው። ያም ሰው ምህረት ያደረገለት አለ። ጌታም ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ በማለት መለሰለት። ወዳጅህ የወደቀው እና ርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ነው ማለቱ ነው። ከላይ ባለው ታሪክ ድንገት አንድ ወዳጁ በእኩለ ሌሊት እንደመጣበት ይናገራል። ተርቧል፣ ደክሟል የወዳጁን ርዳታ ይፈልጋል። እግዚአብሔር በተለያየ ሁኔታ እንድናገኛቸው የሚያደርጋቸውን ሰዎች በቸልታ ማለፍ አይገባንም፣ ምናልባት እንደወደቀው ሰው ርዳታ የሚፈልጉበት የውስጥ ቁስል ያላቸው ይሆናሉ። ከሰላም ጌታ ጋራ ልናገናኛቸው ይገባል።

ለ. <u>በእኩለ ሌሊት</u>

እኩለ ሌሊት በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶ እናነባለን። ይህም ከባዱ የእንቅልፍ ሰአት በመሆኑ ነው። ሰው ምንም ለማድረግ የማይፈልግበት እንቅልፍ የሚጫጫንበት ሰአት ነው። በተጨማሪም ሰው ወደ ውጭ የማይወጣበት አደገኛ ሰአት ነው። ይህ ሰው ግን ወደ ቤቱ ለመጣው ወዳጁ በአስፈሪ ሰአት መምጣቱን ነግሮ ጾሙን ሊያሳድረው ሲችል ሳለ፣ ወደርሱ የመጣው ወዳጁ በድካምና በርሀብ ሆዱ እንዲተኛ አልፈለገም። ስለዚህ በእኩለ ሌሊት፤ በሚያስፈራ ሰአት እንጀራ ሊፈልግለት ቤተሰቡን ጥሎ ጨክኖ ወጣ።ይህ የሚያሳየው የራስን ምቾት ትቶ እንቅልፍን ሰውቶ መማለድ አንዳለብን ነው። ሰለዚህ ስለምናውቃቸው ስላልዳኑ ወዳጆቻችን መማለድ ይኖርብናል። ይህም የሚያስከፍለን ነገር የራሳችንን ምቾት ስለ ጌታ ፍቅር ተወት ማድረግን ብቻ ነው።

ሐ. <u>የሚያቀርብለት የለውም</u>

ጸሎት ሁሉ አለን ለሚሉ ሰዎች አይደለም። በተቃራኒው ባዶነት ለሚሰማቸው የጌታን ርዳታና ጸጋ ለሚፈልጉ ነው። ጌታ ኢየሱሰ የሰጠው ሌላው የጸሎት ምሳሌ ደግሞ፤ ሁለት ሰዎች በመቅደስ ይጸልዩ ነበር አንዱ ፈሪሳዊ ሌላው ቀራጭ ነበር። ፈሪሳዊው ያደረገውን ነገር እየዘረዘረ እጾማለሁ፣ አስራት አወጣለሁ ወዘተ እያለ ጽድቁን ይቆጥር ጀመር፤ ቀራጩ ግን የማይገባኝ ነኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ጀመር። ከፈሪሳዊው ይልቅ ይህ ቀራጭ ጻድቅ ሆኖ ተመለሰ። በዚህ ታሪክ ላይ የተጠቀሰውንም ሰው ወደ ቤቱ ለመጣው ለተራበው ወዳጁ የሚያቀርብለት ማጣቱ በእኩለ ሌሊት ከቤቱ አሰወጣው። ሁሉ ወዳለው ወዳጁ እንዲያስብና እንዲሄድም አደረገው። ዛሬ ብዙ ርዳታ የሚፈልጉ በዙሪያችን አሉ፣ ለነርሱ የሚሆን መልስ የለንም ይሆናል። መልስ የለንም ብለን ግን ዝም ብለን እንቀመጥ። ነገር ግን ሁሉ ወደሞላው ወዳጃችን ወደጌታ እየሱስ ለምልጃ እንገስግስ። ጌታ ለሁሉ ጥያቄ መልስ አለው። በመንፈስ ድሁች የሆኑ ብፁአን ናቸው ይጠግባናሉና።

መ. <u>ያንኳኳ ጀመር</u>

ይህ ሰው ሔዶ በዚያ በእኩለ ሌሊት የወዳጁን በር ሳያቋርጥ ያንኳኳ ጀመር። ወዳጁ ሊሰጠው የማይፈልግ እንኳ ቢሆን እንዳይረበሽ ሲል ለመክፈት እስኪገደድ ድረስ ማንኳኳቱን ቀጥሎአል። ጌታ በሉቃስ 18 ላይ ስለ አንዲት ፍርድ ስለምትፈልግ ሴት ሲናገር ወደ ዳኛው እየሄደች ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር፣ እርሱ ግን ሊረዳት አይፈልግም ነበር፣ ግን እርሷ እየተመላለሰች ስላስቸገረችው ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርዳላታለሁ አለ። ይህ የሚያሳየን በጸሎት መጽናትን እና  ጌታ እስኪመልስ ድረስ ልመናችንን ያለማቋረጥን ነው። ጌታ በማያያዝ ለሚወዳቸው ወደርሱ ለሚጮሁ ምርጦቹ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል ብሎአል። ጌታ እንደዚያ ክፉ ዳኛ አይደለምና!!! በዚሁ ክፍል በቁጥር 9 ላይ ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፍትላችሁማል። በማለት ለሚያንኳኳ የሚከፍት መሆኑን ጌታ ቃል ገብቷል።

ጌታ ለጠፉት የሚያስቡትን፣ በምልጃ ጸሎት የሚተጉትን ከመጠየቅና፣ ከመፈለግ አልፈው እስኪከፈት ድረስ ሳይደክሙ የሚያንኳኩ የምልጃ ሰዎችን ባዶአቸውን አይመልሳቸውም።

**ግን ጌታ ይህን አይነት የእምነት ጸሎት ዛሬ ከእኛ ያገኘው ይሆን?**